# ሸሙጥ

እንዳመቻት የምትወጣ ነፃ ጋዜጣ

ጥቅምት 1970  አ.ም.

## እየታገልን እናሸሚጥጣለን - እያሸሚጠጥን እንታገላለን

**ሸሙጥ ዜና አገልግሎት** (ሸዜናአ) ዴሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ፣ ባስቸኳይ፣ አሁኑኑ....ሲል የቆየው ታጋይ ሁሉ ከዚህ የትግል መድረክ ከወረደ በኋላ ክህደቱን ለመሸፈን አዳዲስ መፈክሮች እፈለሰፋለሁ እያለ ምላሱ ይቆላለፍ በት ጀምሯል። አዲሱ የጊዜው መፈክር? "ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ በትግላችን!" የሚል ነው።

አዲሱ መፈክር እንደተሰማ በሸሙጥ ዝግጅት ክፍል አካባቢ ትንሽ ውዥንብር መፍጠሩ አይቀሬ ነበር። ከዚያ ማ ሸሙጥ ያለፉትን ሶስት አመታት ጉዞ ዘወር ብላ ስትቃኝ እውነትም በተለይ ከየካቲት 1966 አ.ም. ወዲህ የተጧጧፈ የልመና ወቅት ውስጥ ገብተን እንደነበር ተረዳች። ሸሙጥ ይህ ነገር እንደተገለፀላት ወዲያውኑ የትግል ስልት ለውጥ አድርጋለች። እስከዛሬ እንደምታደርገው እያሸሚጠጠች መለመንን ትታ ለትግል ቅድሚያ በመስጠት እየታገለች ማሸ ሚጠጥን መርጣለች። ለማንኛውም የዚችን "ዴሞክራሲ በትግላችን" የምትል አዲስ መፈክር ታሪክ ሪፖርተራችን በት ግል ስልት አራማጆች ማለትም በሰደድ፣ ማሌሪድና ወዝ ሊግ አካባቢ ሰርጎ ገብቶ ባጠናቀረው ሪፖርት በመመርኮዝ ያ ቀረበልንን ሰነድ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

### አይ አልበዛም?! .........ዴሞክራሲስ በትግላችን!

አብዮት አብዮት ብለን ወደ ፈጣሪያችን አዝነን
ስንት  አመት ሙሉ ፆመን...ስንት አመት ሙሉ ፀልየን
ቸሩ ፈጣሪያችን ሰምቶ.....አብዮታችን ፈንድቶ
ይኸው ታዲያ የካቲት ላይ አገኘን
አብዮት አብዮት ብለን ለምነን!
ከዚያስ?
ከዚያማ ስድስት ወር ሱባኤ ገብተን
ንጉሰ ነገስቱን ተማጥነን
ሃይለ ስላሴ እግር ስር ወድቀን
በፈጣሪ ይውረዱልን ብለን ለምነን
እሳቸውም አዝነው፣ አዝነው፣ አዝነው
ምስኪኖች ! ያውላችሁ አትጨቅጭቁኝ ብለው
ብቻ እዚች ላይ ዙፋኑ
በስተግራ ተሰብሯል ከጎኑ
ስትቀመጡበት አትዝናኑ
ብለው ያውም ምክር ሁሉ ለግሰው
ቤት ያፈራው ነው ብለው
ትራስ ስር ከነበረው
መቋቋሚያ ገንዘብ ትተው
ልመናችንን ሰምተው አዝነውልን
በርህራሄ ከዙፋን ወረዱልን!

ከዚያስ?
ከዚያማ እርሶ አደሩ ሁሉ ነቅቶ
ወደ ፈጣሪው ይዘን ተደራጅቶ
ተብሎ....60 ሽህ ወጣት ዘምቶ
ድሃው ሁሉ በያለበት ከወጣቱ ጋር ሆኖ
ወደ ፈጣሪው አዝኖ፣ አዝኖ፣ ለምኖ
ምድረ ባለርስት ሁሳ
ከጢሰኛው ጋር ሆኖ
እሱም በበኩሉ ባለፈው በሰራው አዝኖ
በሉ እሺ ይሁንላችሁ...ያውና
ከናንተ አይብስብኝምና
ብሎ ፈቅዶልን
መሬት ላራሹ ሆኖ
ነፃ ወጣን ባለርስት ተለምኖ!
ከዚያስ?
ከዚያማ መኪና ለምነን
ወደ ከተማ መጥተን
"በግዜር ትርፍ ቤት ያለህ ና ወዲህ በለኝ" ብለን
ዞረን፣ ዞረን፣ ዞረን፣ ዞረን
አምስት ወር ሙሉ ተንከራተን
ይህንን ነገር የወሬ ወሬ
ትርፍ ቤት ያለው ሁሉ ሰምቶ
እንዴት?...ብቻየን ይህን ሁሉ
ብሎ አዝኖ ተፀፅቶ
እሱም እንደ ባለርስት
በሉ ከናንተ አይብስብኝም ብሎ
"ኑ ውሰዱ ያው ትርፍ ቤት" ተብለን
እንዲህ ሆኖ ቤት አገኘን ለምነን!
ከዚያስ?
ከዚያማ እረ ስንቱ ስንቱ!
ብቻ እኛ ለምነን ባገኘነው
የምቀኛው ብዛቱ!
ኢህአፓና ኢዲዩ
እንደኛ መለመናቸውን ትተው
እኛ ለምነን ባገኘነው
በምቀኝነት ተነሳስተው
ቢያስቸግሩን፣ ቢቸግረን
አውግዘን፣ አውግዘን፣ አውግዘን
"እንዴ እንዴት ነው?! አስታግስልን እንጂ" ብለን
መልሰን ወደ ፈጣሪያችን አዝነን

ወደኋላማ እንዲያውም ጭክን ብለን
"አውድማቸው!" ብለን ፈጣሪያችንን ተማጥነን
ያው ብን አሉልን ደስ አለን
እረ ስንቱ ስንቱ!
ሶስት አመት ልመና ስንት አሳየን!
ከዚያስ?
ከዚያማ አብዮት አገኘንና፣ መሬት አገኘንና
ቤት ንብረታችን ተሚልቶ ምቀኞቻችን ተነኑና
ይኸ ሁሉ ልብ አርጉ ....በልመና
አንድ ቀን ቁጭ ብለን ስናወራ
ቅንጦት አማረንና
እስቲ ደሞ ምን እንለምን?
አልንና
አሰበን...አሰበን...አሰበን
"እስቲ ዴሞክራሲ እንለምን" ብለን
ዴሞክራሲ መለመን እንደ ጀመርን
"አቤት ልመና መሰልቸቱ! ሁሌ የሰው እጅ ማየቱ"
አልንና
ታክቲክ እንለውጥ ብለን
አዲስ ታክቲክ
ፈልገን፣ ፈልገን፣ ፈልገን
አዲስ መፈክር እምቢ ቢለን
እንደገና ወደ ፈጣሪያችን አዝነን
"እባክህ ፈጣሪ በፈጠረህ...አዲስ መፈክር" ብለን
ለምነን...ለምነን...ለምነን
ሰማይ ቤት ተሰምቶ ፀሎታችን
አዲስ መፈክር ወረደ ካምላካችን
"አይ አልበዛም?! ዴሞክራሲስ በትግላችን!"
የሚል መፈክር ተቀብለን
"ያውላችሁ ይህን ይዛችሁ
ለምኑ" ተብለን
እሰይ! እኛም ስልት ለወጥን
ታድለን!!!!

**ልመናችን ተሰምቷል! እናሸንፋለን!!**

ነ.ጎ. ኤደን ደቡብ የመን ጥቅምት 1970 ኢ.ም.